MIDROC Newsletter

Special Issue # 56

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

Special Issue # 56 August 2018

# የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ያልተዘመረላቸው የበጎ ተግባር ጀግና

የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ መስከረም 2 ቀን 2000 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መንግሥት ‹‹ለማይዘነጋ ውለታዎ›› የሚል ስያሜ የታተመበት የወርቅ ኒሻን በተሸለሙበት ወቅት ባደረጉት ንግግር ‹‹አገር ለማልማት ባለኝ አቅም ያደረግሁት ሁሉ ገና ስላላረካኝ ለወደፊቱ ብዙ ቀጣይ እቅዶች አሉኝ::›› ‹‹ከህልሜ አንዳንዶቹ ተሳክተዋል አንዳንዶቹ ገና አልሞሉም:: እነሱን ለማሟላት እየሞከርኩኝ ነው›› ማለታቸው አይዘነጋም::

አገር ወዳድ አዛኝ፣ ሆደ ሰፊ፣ ለጋስ የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ‹‹አልረካሁም›› የምንግዜም ቃላቸው ነው!::

ሼህ ሙሐመድ ሁሴን ሥራን የሚያስቀድሙ የቁርጥ ቀን ልጅ እና በትውልድ አገራቸው ውስጥ ባፈሰሱት መዋዕለ ነዋይ ከ74 በላይ ኩባንያዎችን በመክፈት 100,000 ሺህ ያህል ሠራተኞችን የሚያስተዳድሩ ወደር የማይገኝላቸው ባለሀብት ለመሆናቸው እኛ ምስክሮች ነን::






ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር / ፕሬዚዳንት ከቴክኖሎጂ ግሩፑ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር

‹‹ታላቁ የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ኢንቨስተር›› በሚል ስያሜ ጥቅምት 10 ቀን 2010 ዓ.ም. ከሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ሽልማት በተበረከተላቸው ወቅት ሲናገሩ ‹‹የእኔ ምኞት በሕይወት እያለሁ ይህች ደሀ አገር የሚለው ስሟ ተለውጦ ራሳቸውን ችለዋል የሚል ቃል እንድሰማ ነው›› ‹‹የኔ ራዕይ ሁሉም ሰው በልቶ ጠጥቶ እንዲኖር ነው›› በማለት ቃላቸውን በተግባር የተረጎሙ ያልተዘመረላቸው የበጎ ተግባር ጀግና ናቸው፡፡

ህጻናት ተራቡ ሲባል የሚሰጡት ሳያጡ የዕንባ ቋታቸው ሀዘናቸውን መሸከም አቅቶት የሚያነቡ፣ ልቡን ከታመመው፣ አደጋ ከደረሰበት፣ ፊቱን ከተቃጠለው፣ ከተፈናቀለው፣ ከተራበው፣ ከታረዘው፣ መማር ከሚፈልገው እና በሌሎችም ልዩ ልዩ አገራዊ ጉዳዮች ፈጥነው አለሁ የሚሉ፤ በተለይም አገር የኢኮኖሚ እና የዶላር እጥረት ሲገጥማት መፍትሄ የሚሆኑ፤ የምንወዳቸው የመንናፍቃቸው ሼህ ሙሐመድ፤ እውነትም ያልተዘመረላቸው የበጎ ተግባር ጀግና መባል ሲያንሳቸው ነው፡፡

ለዚህም ነው ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር/ ፕሬዚዳንት ጥር 26 ቀን 1996 ዓ.ም. የዘውዲቱ ሆስፒታል ችግርን ለማቃለል የህንፃ ግንባታውን ሥራ በነጻ ለመሥራት በተስማሙበት ወቅት ‹‹እኛ እየረዳን ሳይሆን ዕዳ እየከፈልን ነው፡፡ እያገለገልን እንጂ እየሰጠን አይደለም›› በማለት ለብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ለመፍጠር የቻሉት የሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲንን  አደራ በተግባር እየፈጸሙ እንደሆነ የገለጹት፡፡



*የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በተለያዩ ጊዜያት ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል*



*የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በሚሊኒየም አዳራሽ በመስከረም ወር 2003 ዓ.ም. በነበረው የህዳሴ ግድብ ግንባታ የቦንድ ሠርተፊኬት ርክክብ ሥነ ሥርዓት ወቅት*

# ‹‹አገርን ማልማት የዜግነት ግዴታዬ ነው፡፡››

የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን
አሊ አል-አሙዲ
ጳጉሜ 3 ቀን 1999 ዓ.ም.



- በዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ በዋሽንግተን ከተማ የሚገኘው የኮርፖሬት ካውንስል ኦፍ አፍሪካ ዲሴምበር 16,2014 ላይ በተካሄደው ጉባዔ ላይ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ባለቤትና ሊቀመንበር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በአፍሪካ የዓመቱ ታላቁ የቢዝነስ ሰው በሚል ዕውቅናና ሽልማት ሲሰጣቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለምን እንደሚያረጉ ሲናገሩ ‹‹በአገሬ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖርና ዜጎቿ ከፍተኛ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ማየት የዘወትር ምኞቴ ነው፡፡ ሁሌም እኔና ኩባንያዎቼ ለኢትዮጵያውያንና ለአፍሪካውያን የሥልጠናና የትምህርት ድጋፍ እናደርጋለን፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ኩባንያዎቼ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ተሳታፊ በመሆናቸውና በአፍሪካም የሚደረገው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ያስደስተኛል፡፡ ይህንን ሽልማት በሠራተኞቼና በኩባንያዎቻችን ስም ስቀበል ደስታና ኩራት ይሰማኛል›› ነበር ያሉት፡፡
- በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በጉጂ ዞን የምትገኘው ሻኪሶ በልማት፣ በጤናና፣ በትምህርት ዕድገት ወደ ኋላ መቅረቷን በማስረዳት እገዛ ለጠየቀው የጉጂ ዞን ሕዝብ የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ እቦታው ድረስ በመገኘት፣ ለኦሮሚያ ክልልና ለአገሪቱም ጭምር የጥበብ ባለሙያዎችን ማፍራት የሚችል አንድ ትልቅ የሁለገብ የሙያ ትምህርት ተቋም (ቮኬሽናል) ኮሌጅ በዞኑ ለሚገኙ 15ቱም ወረዳዎች ለትምህርት መስፋፋት እገዛ እንዲያደርግ፣ ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ሚሊዮን ብር ለመስጠት ጥር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በገቡት ቃል መሰረት የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዜኪዩቲቭ ኦፊሰር/ፕሮዚዳንት ዶ/ር አረጋ ይርዳው በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር የፕሬዝዳንቱ ቢሮ በተደረገ ሥነ-ሥርዓት፡-
- ለኮሌጁ ማሠሪያ 12 ሚሊዮን ብር፣
- በጉጂ ዞን ለሚገኙት 15 ወረዳዎች ለእያንዳንዳቸው 1 ሚሊዮን ከኮሌጁ ህንጻ ማሠሪያ ጋር በድምር 27 ሚሊዮን ብር በቼክ በወቅቱ ለነበሩት የክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ አባዱላ ገመዳ አስረክበዋል፡፡
- በናዝሬት ከተማ መግቢያ ላይ ባለው ክፍት ሥፍራ በ64 ሄክታር ክልል ላይ ለተገነባው ሐውልት እና በዙሪያው ላሉት ቋሚ የኤግዚቢሽን ማዕከል፣ የቲያትር አዳራሽ፣ የተለያዩ ቢሮዎች፣ የምርምር ማዕከልና ቤተ-መጻሕፍት እንዲሁም የመዝናኛ ሥፍራዎችና የእንግዶች ማረፊያ ለተገነባበት፤ የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ 50 ሚሊዮን ብር በመለገስ ላደረጉት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በወቅቱ ከነበሩት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት አቶ አባዱላ ገመዳ ምሥጋናና ሽልማት ተቀብለዋል፡፡
- የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ሊቀመንበራችን ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ለመሆናቸው የቀረበላቸው ሽልማት ይመሰክራል፡፡

**ለመሆኑ ሊቀመንበራችን ምን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተው ነው፤ ዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበር (ፊፋ) በ202 አባል አገሮቹ ባደረገው ምርጫ ከ45 ልዩ ተሸላሚዎች መካከል ልዩ የሜሪት ተሸላሚ ያደረጋቸው?**

**ሊቀመንበራችን ለኢትየጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን የውጭ አሰልጣኝ በመቅጠር፣**

- የቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብን ዓመታዊ በጀት በመሸፈንና የተጫዋቾችን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ሙሉ የህክምና ወጪ በመሸፈን ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማህበር (ፊፋ) ልዩ የሜሪት ሽልማት ሊያበረክትላቸው ችሏል፡፡
- በሌላ በኩል ደግሞ በተፈጥሮ የአየር መዛባት ምክንያት ድርቅ ባስከተለው አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን ስቃይ ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት በሚደረግበት ወቅት በወቅቱ ከነበሩት የሚድሮክ ሠራተኞች የተውጣጣውን 2,142,551.50 ብር አንድ ብር የራሳቸውን ጨምረው

በአጥፍ በመለገስ በጠቅላላው ከ4.2 ሚሊዮን ብር በላይ ለተጎጂ ወገኖች እንዲደርስ በሊቀመንበራችንና በሠራተኞች ስም ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የዕርዳታ ሰብሳቢ ኮሚቴ አስረክበዋል፡፡

- በአዲስ አበባ ከተማ በ47 ሚሊዮን ብር ወጪ የተሠራው የአፍሪካ ፓርክ ግንቦት 20 ቀን 1997 ዓ.ም. በተካሄደ ፕሮግራም ተመርቆ ሲከፈት የፖርኩ ግንባታ ሙሉ ወጪ የተሸፈነው በሊቀመንበራችን በሼህ ሙሐመድ ልግስና ነው፡፡

- **‹‹ፖርኩ ለምወዳት ኢትዮጵያና ለመላው አፍሪካ ህዝቦች የተበረከተ ስጦታ ነው››**

*የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ*

- ከምንም በላይ ሰው ተኮር የሆኑ ተግባራቶቻቸው ጎልተው የሚታዩት ሼህ ሙሐመድ ጧሪ ያጡ አረጋውያንን ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ በገንዘብ እና አምቡላንሶችን በመለገስ ላደረጉት የላቀ አስተዋጽኦ ሲጠየቁ ‹‹ተወኝ›› ገና ምን ተደረገ እና ነው በማለት መልስ የሚሰጡ እውነተኛ ለጋስ እና የተግባር ሰው አስተዋጽኦ ከብዙ በጥቂቱ ለግንዛቤ ያህል ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

- ለኦሮሚያ ክልል ተፈናቃይ ወገኖች 40 ሚሊዮን ብር እንዲሁም ደብረ ዘይት ለማረፊያ የሚሆን 121 ቤቶች የሚድሮክ መንደር ምንግዜም ወንድማቸው በሆኑ ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር /ፕሬዚዳንት አማካኝነት አሠርተው ቁልፍ ያስረከቡ፣

- ለህዳሴ ግድብ ግንባታ 1.5 ቢሊዮን ብር ቃል በመግባት እንደውም ለዚህ ግድብ ግንባታ የለበስነውን ልብስ እንኳን ብንሸጥ የሚያንሰው ነው በማለት የተናገሩ፣

- በወልድያ ከተማ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ‹‹ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ስታዲየምና የወጣቶች ማዕከል›› በ567,890,000 ብር ገንብተው ያስረከቡ፡

- እኚህ የቁርጥ ቀን ልጅ አዲስ አበባ ‹‹የአፍሪካ ህብረት ዋና ከተማ›› ለመሆን ሟሟላት ይገባታል የተባለውን ቃል ለመፈጸም በፍጥነት የጎደላትን 60 ዘመናዊ መርሴዲስ አውቶሞቢሎች በማስመጣት አገራቸው የአፍሪካ መዲና እንድትሆን ያደረጉ፣

- በ84 ሚሊዮን ብር ሃያ ሺህ ሰው የሚይዝ ደረጃውን የጠበቀ የሚሊኒየም አዳራሽ ያስገነቡ፣

- ከሸራተን አካባቢ ለተነሱ አምስት መቶ ቤተሰቦች የተሟላ ቤት በመሥራት በነፃ የስረከቡና ከዚህ ጐን ለጐን ሼህ ሙሐመድ በጤናው ዘርፍም፣

- ለልብ ህሙማን ሆስፒታል መገንቢያ 33 ሚሊዮን ብር የለገሱ ለዚህም በጎ ሥራቸው ምስጋና የተቸራቸው ናቸው፡፡

- በቆሼ አካባቢ አደጋ ለደረሰባቸው ቤተሰቦች ማቋቋሚያ 40 ሚሊዮን ብር የለገሱ፤

- በምግብ እጦት ለተቸገሩ በሺህ ለሚቆጠሩ ህፃናት ተማሪዎች 26 ሚሊዮን ብር በዓመት በመመደብ ለወገናቸው ልጆች የወደፊት እጣ ፋንታ አለኝታ የሆኑ፣

- በኢትዮጵያ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ተከስቶ የነበረውን ርሃብ ለመቀነስ ከውጪ ሀገር እህል እንዲገባ በማድረግ እና አገራችን ገጥሟት ለነበረው የዶላር እጥረት አንድ መቶ ሺህ ዶላር በመለገስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፣

- ሊቀመንበራችን ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ባደረጉት ከፍተኛ እገዛና ዕርዳታ ብሔራዊ ቡድናችን ውጤት እንዲያስመዘግብ ማድረጋቸው፡፡ በብሔራዊ ቡድኑ በሊቀመንበራችን ስም በተሰየመውና ለሶስት ዓመት ስፖንሰር ባደረጉት የምሥራቅና መካከለኛ አፍሪካ አገሮች ‹‹የአል-አሙዲ ሲኒየር ቻሌንጅ›› ለሁለተኛ ጊዜ ሻምፒዮን ለመሆን መብቃቱ ለቡድኑ እያንዳንዱ አባላት የገንዘብ ሽልማት ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

- አገራችንን ወክለው በአትሌቲክስ የተሳተፉትን ሼህ ሙሐመድ የግል ጀታቸውን በመላክ ወደ አገራቸው ከማምጣት ባሻገር የ165 ሺህ የአሜሪካን ዶላር በመለገስ፣

- ከሳዑዲ አረቢያ ከስደት ተመላሽ ወገኖችን 10 ሚሊዮን ብር በመስጠት ከመርዳት ባሻገር በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ከኬጂ እስከ 8ኛ ክፍል እንዲማሩ ለ100 ልጆች እድል በመስጠት ይህንኑ ኃላፊነትም ለዶ/ር አረጋ ይርዳው ለዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት መስጠታቸው፣

- ለእናት ወግ ዕርዳታ ማህበር 40 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ በመለገስ፣

- ለቡና ስፖርት 1 ሚሊዮን ብር በመስጠት፣

- ካሚላት በደረሰባት የአሲድ መደፋት ችግር ፈጥነው በመድረስ፣

- ለኤች አይ ቪ ኤድስ ህሙማን ድጋፍ 10 ሚሊዮን ዶላር ለ16ኛው ዓለም አቀፍ የኤድስ ኮንፈረንስ ላይ በመለገስ፣

- ለብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን ለሴቶችና ለወንዶች 20 ሚሊዮን ብር በመለገስ፣

- ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ 90 ሚሊዮን ብር በመለገስ ያደረጉትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በዚህ አጭር ጽሁፍ የረዥም ጊዜ ያልተነገረላቸው የበጎ ተግባር አምባሳደርነት ታሪክ ዘርዝረን አንጭርሰውም፡፡

እንደው ከብዙ በጥቂቱ ስለ እሳቸው በጎነት የተጻፈውን ሁሉ ሳይሆን የማስታውሰውን ብቻ አውጥቼ ልጻፈው፤ የበጎ አድራጎት ጀግናችን፣ ለአርቲስቶች እና ለታዋቂ ሰዎች አደረጉ የተባለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አልደግመውም ምክንያቱም ለቀባሪው ማርዳት ስለሚሆን ነው፡፡ ቢሆንም ከብዙው በጥቂቱ ስማቸውን ጠቅሼ አልፋለሁ፡፡

ለዓሊ ረዲ የቀደሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን

ግብ ጠባቂ፣ ለዶ/ር ሚኪያስ ሻምቦ፣ ለስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ፣ ለታዋቂው አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ፣ እና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ዜጎቻችን ችግር ፈጥነው በመድረስ ያደረጉት ልግስና ምን ግዜም ሲዘከር የሚኖር ነው፡፡

በአሁን ሰዓት ለአገር፣ ለወገን የሚጠቅሙት የበጎ ተግባር አምባሰደር የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ እንዲፈቱልን ስንመኝ ነበር፡፡ ይህም ምኞታችን ጊዜ አስቆጥሮ ይፈታሉ እያልን ስንጠብቅ ሰባት ወር ሞላን፡፡ የመፈታታቸውን ዜና ለመስማት  ግንቦት 11 ቀን 2010 ዓ.ም ሁላችንም ለጉብኝት ሳዑዲ ዓረቢያ የሄዱት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ፤ ሳዑዲ በእስር የሚገኙትን ሊቀመንበራችንን የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ በማስፈታት ይዘዋቸው ይመለሳሉ ብለን ጓጉተን ስንጠበቅ ነበር፤ ድንገት ከወደ ሚሊኒየም አዳራሽ የመጣው የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ድምጽ ግማሽ ደስታ ይዞ ብቅ አለ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትራችን ስለ ሊቀመንበራችን መፈታት ከሳዑዲ መንግሥት ቃል እንደተገባላቸውና ትንሽ ጊዜ ቢቆዩ ነው እንጂ ይፈታሉ ብለው አጽናኑን፡፡ እኛም ይህንን ቃል ተስፋ አርገን ስንጠብቅ ጊዜ ጊዜን እየወለደ ብዙ ቅዳሜዎችን አሳለፍን፡፡ ለዚህ ነው ቀደም ብሎ በሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ቺፍ ኤግዚኪዩቲብ ኦፊሰር/ፕሬዚዳንት በዶ/ር አረጋ ይርዳው አመራር የተጀመረው ‹‹ሼህ ሙሐመድ ይፈቱልን›› ዘመቻ በሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ሠራተኞች የተቀጣጠለው፡፡ ዛሬም ሁላችንም በይፈቱልን ዘመቻችን እኚህ ያልተዘመረላቸው የበጎ ሥራ አምባሳደር፣ የቁርጥ ቀን ልጅ ይፈታሉ የሚለው ግማሽ ተስፋ ሙሉ መሆን አለበት እንላለን፡፡






*ዶ/ር አረጋ ይርዳው በመቻሬ ኮርፖሬት ሴንተር መቻሬ ሜዳ "ሼህ ሙሐመድ ይፈቱ" የሚለው ዘመቻ በይፋ መጀመሩን በማስመልከት ንግግር ሲያደርጉ*

# ስለ ሼህ ሙሐመድ ከተጻፉ ግጥሞች መካከል

## የቁርጥ ቀን ደራሽ!!

ክቡር ሼህ ሙሐመድ በድንገት ታገቱ፣
የሚለውን ዜና ሰምቶ በየቤቱ፣
ሁሉም ተጨነቀ ወጣት አዛውንቱ፣
የደሆቹን አባት የኢትዮጵያን አለኝታ፣
በማረፊያ ጊዜህ የማታ የማታ፣
ለምን አገተችህ ሳዑዲ አንተን ጠርታ፣
በቸገረው ጊዜ ለዋለ ውለታ፣
መች እንዲህ ነበረ የክብር ስጦታ፣
አለች ኢትዮጵያም በጣም ተቆጥታ፡፡
ሠራተኛው አዝኖ አንዱ አንዱን ሲያፅናና፣
ዶክተር ፈጥነው መጡ ዜናውን ሰሙና፣
ጊቢ እንደደረሱ ወደ አዳራሽ ገብተው፣
እኛን አረጋጉን መድረክ ላይ ወጥተው፡፡
ከኛ የሚጠበቀው እሱም ደስ የሚለው፣
ፌስ ቡክ የሚለውን ወሬ ሳታወሩ
እየፀለያችሁ ሥራችሁን ሥሩ፣
ብለው በአፅንዖት ቆመው ተናገሩ፣
እኛም መመሪያውን በጥሞና ሰምተን፣
ይሄው እንሠራለን ሁሉን ለአምላክ ሰጥተን፣
በሥራ ላይ ያለ ከሃምሳ ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣
ሦስት መቶ ሺህ ያልፋል ከነቤተሰቡ ከቆላ እስከ ደጋ፣
እናም ይኼ ሁሉ የሱን እጅ ጠባቂ መሆኑ አይዘንጋ፣
ተስፋን ስንቅ አድርጎ ምንም ቢረጋጋ፣
ቀንን ቀን ሲወልደው የመሸው ሲነጋ፣
ትኩረት ካልተሰጠው የኋላ የኋላ ያስከፍላል ዋጋ፡፡
የወለድናቸውን ቆመን እንድንድር፣
እድሜ ጤናን ሰጥቶት አባታችን ይኑር፣
ቤተሰቡም ይብዛ ይባረክ በፍቅር፡፡
ነገ ዛሬ ሳትል ቆሎ እንድትፈታ፣
እኛ እንፀልያለን ከጧት እስከ ማታ፣
አምላካችን ይርዳህ አንተ ብቻ በርታ፡፡
ይድረስ ለሳዑዲው ልዑል አልጋ ወራሽ፣
አልጠራጠርም አትረሳም በጭራሽ፣
ሙስሊም ወገኖችህ በዓለም ሲሰደዱ፣
ሰላም ወዳለባት ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ፣
ብለው ሲልኳቸው ነብዩ ሙሐመድ
አይዟችሁ የሚል ሲያጡ ወዳጅ ዘመድ፣
ሀገሬ በፍቅር መግቢያ በሯን ከፍታ፣
ኑ ወደ እኔ እያለች እጆቿን ዘርግታ፣
ቤት ለእንግዳ ያለች ካዓለም ተለይታ፣
በዘር በሐይማኖት ሳትለይ በቀለም፣
በእምነቷ የኖረች ፀንታ ለዘላለም፣
ኢትዮጵያ ብቻ ነች ሌላ ማንም የለም፣
እናም ውለታዋን መክፈል የምትችለው፣
የቁርጥ ቀን ደራሽ ልጇን ስትፈታው ነው፡፡
ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚጠባበቀው፣
እሱን በዓይነ ሥጋ እስከሚያይ ጓጉቶ ነው፡፡
በኢትዮጵያዊያን ሁሌ እንድትወሳ
ሙሐመድን ልቀቅ ውለታ ሳትረሳ፡፡

*በላይ ካሣ ለገሰ (ከኤምቢአይ)*
*ሰኔ 2010 ዓ.ም*

## እኔና ብዕሬ

ብዕሬ ንገሪኝ ልጠይቅሽ ዛሬ፣
ታሰሚኝ እንደሆነ እንደወትሮው ወሬ፣
ደስታ አሰሚኝና ልመለስ ዘምሬ፡፡
ድሮ ደስታ ነበር የበዓል ዋዜማ፣
ከኔ ነው? ወይ ካንቺ? ምንድነው የሚሰማ?
እያልኩ ለብዕሬ ብሶቴን ሳሰማ፣
አለችኝ አድምጠኝ አስተውለህ ስማ፡፡
አንተ ሰው ልብ በል እንዳትዘናጋ፣
ሁልጊዜ አይመችም አይሆን አልጋ ባልጋ፣
ይልቅ ለፈጣሪ እጆችህን ዘርጋ፡፡
አንተ የምታስበው ሁልጊዜ ጭማሪ፣
መቼ አንተ ብቻ ሌላም ተባባሪ፣
ተመስግን ካላልከው ባለህ ፍርፋሪ፣
ለወጥ ያደርጋታል ምን ገዶት ፈጣሪ፡፡
መቼ አንተ ብቻ ሁሉም ለራሱ ነው፣
ይህን ሳድረግ አይልም ሁሌ አድርጉልኝ ነው፣
ወዳጄ አስተውለኝ እኔ እውነቴን ነው፣
ይኸው ትሰማለህ ነገ የምታየው ነው፣
ወቅቱን ተመልክተው ሠጥቶ መቀበል ነው፣
ምንም መንገድ የለም አማራጩ ይኸው ነው፡፡
አለችኝ ብዕሬ በተባው ምላሷ፣
እውነትን ታጥቃለች ምንቸገራት እሷ፣
ተመቸኝ ምክሯ ክብርና ሞገሷ፣
መቼም ሰው አይደለች ውለታን አትረሳ፡፡
ቀጠለች ብዕሬ .......
ይልቁን አለችኝ ልምከርህ ወንድሜ፣
ሁሉን አውቀዋለሁ ከአንተ አስቀድሜ፣
ተዓምር ትሰማለህ ፈጣሪ ይስጥህ ዕድሜ፣
ለዚህ ነው አስተውል ያልኩ ደግሜ ደግሜ፡፡
እርሳስ እንዳልመስልህ ተረዳኝ በእርጋታ፣
ኢንተርኔት ኳርኳሪ የፌስቡክ ጋጋታ፣
በወሬ (የምነዳ!) ያውም በአሉባልታ፣
እውነቱን ልንገርህ እኔ የምረታው በላይኛው ጌታ፡፡
ስለዚህ አካሌ ሁሉም ለበጐ ነው፣
በትንሽ ስትጠይቅ ትልቅ ፈጻሚ ነው፣
ሀዘን ቢፈራረቅ ደስታን አብሳሪ ነው፣
ሰው ሁሉ ቢተውህ የማይተው እርሱ ነው፡፡
አለችኝ ብዕሬ ......
እኔም ለብዕሬ እንዲህ ስል መከርኳት፣
ክፋትን እንዳትረጭ እያስጠነቀኳት፣
ቀለም ሆድሽ ይሙላ አንቺም ተባረኪ፣
በጐውን ዘግቢ እውነቱን ተርኪ፣
እውነቱን ጨብጠሽ ውጤቱን አሳኪ፣
ስለ ደጉ ሩህሩህ ልጠይቅሽ እስኪ፣
ጠላት ዓይኑ እያየ ማንንም ሳትነኪ፣
ንገሪ ቢሰሙሽ እውነቱን ተርኪ፣
ያው መራቂሽ እኔው ነኝ አይዞሽ ተባረኪ፡፡
አልኳት ለብዕሬ የሆዴን ዘርዝሬ፣
ብዕሬም አለችኝ .......
ፍጹም እንዳታስብ ተወው ስለሳቸው፣
ሁሉም የሚያጭደው ያው የዘራውን ነው፣
ካንተ የሚጠበቀው ሁሉም ለበጐ ነው፣
ውጤቱ የሚያፈራው በጾም በጸሎት ነው፡፡
ታዲያ ይሄን ጊዜ የፈለገው ይወራ፣
በጭስ ብቻ ያልቃል የውሸት ደመራ፣
አንተም ትሰማለህ እውነቱ ሲጣራ፣
እንዳትጠራጠር የፈጣሪን ሥራ፣
እውነት መሠረት ናት እመን እንጂ አትፍራ፡፡
እንዲህ አለች ብዕሬ በእምባዋ እየጻፈች፣
ግራ ቀኙን አይታ ያው እየታዘበች፣
ፀሎት እንደሚያድን ለሁሉ እያወጀች፣
ብዕሬ እራሷን ለፈጣሪ ሰጠች፡፡
መልሳም እንዲህ አለች ለሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ፣
ፍጹም ደስታና ብስራት ለሚያሰማን፣
እንዲሁ እንደዛሬው በአንድነት ሳይለየን፣
የኢትዮጵያ አምላክ ፈጣሪ ይመስገን፡፡
አሜን!!!

*ተካልኝ ተፈራ ወንድማገኘሁ (ከዋንዛ)*
*ሰኔ 14 ቀን 2010 ዓ.ም.*

*“ሼህ ሙሐመድ ይፈቱ” የሚል ዘመቻ በይፋ በተጀመረበት ዕለት በሥነ ሥርዐቱ ላይ ከተካፈሉ የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ሠራተኞች በከፊል*









## የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች
## Members of the MIDROC Technology Group Companies




### MTG companies are involved in:

**Mining & Exploration; Agro Industry; Education; Real Estate; Air Transport; Customs Clearing; Car Rental & Tourism; Automotive Maintenance; Wood Works; Aluminum Works; Packaging; Retail Service; Metal & Engineering Products, Paints, Fillers & Tiles manufacturing; Glass Bottles, Crates, Poly Bag Products manufacturing; and Management & Leadership Services.**

## "Investment with a mission to be SECOND-TO-NONE"

Tel.: +251-011-371-8900/+251-011-372-6150
Fax: +251-011-371-5988/+251-011-372-6037
P.O.BOX: 5787, Addis Ababa, Ethiopia
Email: contact@midroc-ceo.com

**www.midroc-ethiotechgroup.com**

*በነፃ የሚታደል (Distributed at no Cost)*